የዋሽንግተን ግዛት ለፀባይ ጤና

# የሚጠቅሙ መፃሕፍት




የዋሽንግተን ግዛት የማሕበራዊና የጤና አገልግሎት መምሪያ

የፀባይ ጤናና መሻሻል ክፍል


Washington State Department of Social & Health Services

Transforming lives

ይህ ማንበብ የማይችሉት ቋንቋ ከሆነ እገዛ
እንዲያገኙ እባኮትን በ 1-800-446-0259 ይደውሉ።

Amharic

---

على 1-800-446-0259 للحصول على مساعدة.
إذا لم تتمكن من قراءة هذه اللغة، يُرجى الاتصال

Arabic

---

បើសិនវាមិនមែនជាភាសាដែលអ្នកអាចអានបាន
សូមទូរស័ព្ទ 1-800-446-0259 សំរាប់ជំនួយ ។

Cambodian

---

如果您看不懂這種語言，請電1-800-446-0259 請求幫助。

Chinese

---

이 내용의 글이 귀하가 읽지 못하는 언어로 써여져
있으면 1-800-446-0259로 전화하여 도움을
요청하십시오.

Korean

---

ຖ້າບໍ່ແມ່ນພາສາທີ່ທ່ານອ່ານໄດ້, ກະຣຸນາໂທຫາ
1-800-446-0259 ເພື່ອຂໍຄວາມຊ່ວຍເຫລືອ.

Laotian

---

ਜੇ ਇਹ ਅਜਿਹੀ ਭਾਸ਼ਾ ਹੈ, ਜਿਸ ਨੂੰ ਤੁਸੀਂ ਨਹੀਂ ਪੜ੍ਹ ਸਕਦੇ, ਤਾਂ
ਕਿਰਪਾ ਕਰਕੇ ਮਦਦ ਲਈ 1-800-446-0259 'ਤੇ ਕਾੱਲ ਕਰੋ।

Punjabi

Если данный документ напечатан на языке, на котором вы не можете читать, пожалуйста, обратитесь за помощью, позвонив по телефону 1-800-446-0259.

Russian

---

Haddii aysan tani ahayn luqadda aad akhrin kartid, fadlan wac 1-800-446-0259 si laguu caawiyo.

Somali

---

Si esto no está en un idioma que puede leer, por favor llame al 1-800-446-0259 para recibir ayuda.

Spanish

---

Якщо ви не можете читати цією мовою, зверніться по допомогу, зателефонувавши за номером 1-800-446-0259.

Ukrainian

---

Nếu đây không phải là ngôn ngữ của quý vị, xin hãy gọi số 1-800-446-0259 để được giúp đỡ.

Vietnamese

---

ይህንን መፅሐፍ ማንበብ በሚችሉት ቋንቋ ማግኘት ካልቻሉ አባክዎትን እርዳታ ለምግኘት ወደ **1-800-446-0259** ይደውሉ።

# ወደ የዋሽንግተን ግዛት ለፀባይ ጤና የሚጠቅሙ መፃሕፍት እንኳን በደህና መጡ

**ይህ አገልግሎት በሜዲክኤድ ለሚረዱ ሰዎች ተብሎ የተዘጋጀ ነው። ሜዲክኤድ ውስጥ ያልተመዘገቡ ቢሆንም የሕክምና የአእምሮአዊ ጤና እንዲሁም መድሃኒት የሚያስፈል ገው አገልግሎት ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፥ [www.waHealthPlanFinder.org](http://www.waHealthPlanFinder.org) ይጎብኙ ወይም ወደ 1-800-562-3022 ይደውሉ።**

በሜዲክኤድ የተመዘገቡ ሰዎች በፀባይ ጤና ድርጅት BHO አማካኝነት የአእምሮአዊ ጤና እንዲሁም መድሃኒት ለሚያስፈልገው የፀባይ ጤናም ለሚባለው ሕመም የሚሆን አገልግሎት የማግኘት አጋጣሚ አላቸው። እነዚህ አገልግሎቶች በግዛቱ ሁሉም ቦታዎች ይገኛሉ ከ Clark እና Skamania አውራጃዎች በስተቀር (የእርስዎን BHO ለማግ ኘት www.dshs.wa.gov/BHOcontacts) ን ይጠቀሙ፡፡ የፀባይ ጤና ድርጅት BHO በመረጡት ቋንቋና ፎርማት፥ ማለትም በቃልም በፅሑፍም የሚፈልጉትን መረጃን እርዳታ ሊሰጥዎት ይችላል። ከሚሰጡር አገልግሎት በጥቂቱ ለመጥቀስ ያክል

- በአከባቢዎ ስለሚገኙ የፀባይ ጤና ባለሙያዎች ስም ዝርዝር፡ የሚገኙበት መረጃ፥ በምን ዘርፍ የተካኑ እንደሆኑ፥ እንዲሁም ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጭ በሆነ በሌላ ቋንቋ ስለሚሰጡት አገልግሎት የሚገፅ መረጃ
- አገልግሎት ሰጪው ወይም የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ስለሚያዘጋጀው ተርጓሚ
- ወደ ቀጠሮ ቦታዎ ስለሚወስድዎት የትራንስፖርት መረጃ
- የአዕምሮ ጤና የተሻሻለ ደንብን በተመለከተ መረጃ

## ለምሳሌ እንደ Clark ወይም Skamania አውራጃዎች ባሉ ሙሉ በሙሉ የተዋ ሀደ ቁጥጥር የሚደረግበት የእንክብካቤ ክልል ውስጥ ብኖርስ?

በ Clark ወይም Skamania አውራጃ የሚኖሩ ከሆነ ቁጥጥር የሚደረግበት እንክብካቤ የጤና እቅድ የባህሪያዊ የጤና አገልግሎትዎትን ያስተባብራል እንዲሁም ይከፍላል፡፡ በሜ ዲኬድ እቅድ Plan ውስጥ ያልተመዘገቡ ከሆነ ወይም የትኛው እቅድ እንዳለዎት ካላወቁ ወደ Washington State Health Care Authority በ 1-800-562-3022 ይደውሉ። በግዛቱ ውስጥ ያሉ ሌሎች ክልሎች ሙሉበሙሉ በመዋሀድ ቁጥጥር የሚደረግ ባቸው እንክብካቤ ሲሆኑ https://www.hca.wa.gov/about-hca/healthier-washington/regional-resources ላይ የበለጠ መረጃ ይገኛል፡፡

## የአሜሪካ ህንዶች እና የአላስካ ቀደምት ኑዋሪዎች እንዴት በMedicaid የተሸፈነ የባህሪ ጤና ህክምና አገልግሎቶች ያገኛሉ?

- ለMedicaid ብቁ የሆኑ እራሳቸውን እንደ አሜሪካ ህንዶች ወይም የአላስካ ቀደምት ነዋሪ የሚቆጥሩ ሁሉ ለበህሪ የጤና አገልግሎቶች ለአገልግሎት በሚከፈል በት ፕሮግራም ግዛቷ ተመድባለት:
  - ለ Medicaid ማመልት ወይም ድጋሚ ለማረጋገጥ ወይም፤
  - በጤና እቅድ አፋላጊ ድረ ገፅ ተከታይ ለውጦችን ለማስገባት፡ https://www.wahealthplanfinder.org/_content/Homepage.html
  - የጤና ክብካቤ ባለስልጣን የደንበኛ ጤና አገልግሎት ማእከልን በ 1-800-562-3022, TDD/ TTY ብቻ 1-800-848-5429, 711 (የማስሚ ወይም የመናገሪያ መሳሪያ ለሚጠቀሙ ሰዎች).
- በ Medicaid የተመዘገቡ የአሜሪካ ህንዶች ወይም ቀደምት የአላስካ ኑዋሪዎች የባህሪ ጤና ህክምና ከማንኛውም አስከፍሎ አገልግሎት ከሚሰጥ Medicaid ተመዝጋቢ መጠየቅ ይችላሉ።
- ለአገልግሎት በሚከፈልበት ፕሮግራም ፤አገልግሎቶች BHO ወይም የግዛት ፍቃድ አያስፈልጋቸውም።
- የአካሚ ድርጅቶችን ዝርዝር እዚህ ላይ ፡ያገኛሉwww.dshs.wa.gov/bha/services-american-indians-and-alaska-natives.

ይህንን የማይመለከተው በደቡባዊው ምዕራብ አከባቢ (ክላርክና ስካማኒያ ካውንቲ) ውስጥ የሚገኙት ለሜዲክኤድ ብቁ የሆኑ ነዋሪዎችን ነው፡-

- በደቡባዊው ምዕራብ አከባቢ፥ ለሜዲክኤድ ብቁ የሆኑ የአመሪካ ህንዶች ወይም በአላስካ የሚሆኑ ያገሩ ተወላጆች በማኔጅድ ኬር ኦርጋናይዜሽን (MCOs) አማካኝነት ከጤና እንክብካቤ ባለስልጣን ጋር በተገባው ውል መሰረት መድሃኒት ለሚስፈልገው የሕመም ዓይነት (SUD) የሚሆን አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

**ይህ መፅሐፍ በፀባይ ጤና ድርጅት BHO አማካኝነት የሚካሄደውን አገልግሎት በተመለከተ የሚከተሉትን ያብራራል፡-**

- የባህሪ ጤና አገልግሎት ማግኘት የሚቻለው እንዴት እንደሆነና በድንገኛ ሁኔታ ምን ማድረግ እንደሚገባ፥
- በግዛቱ ባለው የማሕበራዊና የጤና አገልግሎት መምሪያ - የባህሪ ጤናና ማገገሚያ ክፍል (DBHR) የሚገኝ የባህሪ ጤና አገልግሎት፥
- ተጨማሪ የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች
- መብትዎና ግዴታዎት
- እርስዎና ቤተሰብዎ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንዴት ሊትረዱን እንደምትችሉ፥
- ስለ የሕክምና እንክብካቤ የሚገልፅ መረጃ፥
- በአገልግሎቱ ካልረኩ ምን ማድረግ እንደሚቻል፥ እና
- እርስዎ ማወቅ ያለብዎት ሌሎች አስገፈላጊ መረጃዎች።

መንግስት ከሚደጉማቸው የፀባይ ጤና አገልግሎት ጋር ስለሚያያዙ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት የዋሽንግተን የተከለሰ ሕግ (RCW) ላይ ምዕራፍ 70.96.A, 71.05, 71.24, እና 71.34 በhttp://apps.leg.wa.gov/rcw/ላይ ይመልከቱ።

ለሜዲኬድ ተመዝጋቢዎች ስለሚሆን የDBHR የፀባይ ጤና ስርዓትና አገልግሎት ለማወቅ ይህንን ድረገፅ ይጎብኙ፡- www.dshs.wa.gov/bha/division-behavioral-health-and-recovery.

**የዚህን መፅሐፍ የታተመ ቅጂ ከፈለጉ በገፅ 5 ላይ ተዘርዝረው የሚገኙትን የፀባይ ጤና ድርጅቶችን ያነጋግሩ።**

## አማራጭ የቡክሌት ትርጉሞች

If you have questions about any part of this booklet, or need this information in another language or a different format such as American Sign Language (ASL), oral interpretation, Braille or large print, please call us at 1-800-446-0259 or please contact us through our Relay Service (TTY) at 1-800-833-6384 or dial 7-1-1. All accommodations or requests for alternative formats are provided at no cost.

ስለ ዚህ ቡክሌት የትኛውም ክፍል ጥያቄ ካሎት ወይም ይህን መረጃ በሌላ ቋንቋ የሚፈልጉት ከሆነ ወይም እንደ አሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL) የዓፍ ትርጉም፤ብሬል ወይም ትልቅ የፅሁፍ ህትመት ያለ የተለየ ቅርፅ ከፈለጉ በ1-800-446-0259 ላይ ይደውሉ ወይም በማስተላ ለፊያ አገልግሎት (TTY) 1-800-833-6384 ይላኩ ወይም 7-1-1 ላይ ይደውሉ። ሁሉም መስተንግዶዎች ወይም አማራጭ ቅርፆች ያለ ወጪ ቀርበዋል

# የርዕስ ማውጫ


አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮችና መረጃዎች ........................................2

የአገልግሎቶች መረጃ .........................................................4

ምን ምን አገልግሎቶች አሉ? ................................................8

የልጆች የEPSDT መብቶች ............................................... 12

የሜዲክኤድ የፀባይ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ
እንደመሆንዎ መጠን ያለዎት መብት ........................................ 14

የአእምሮ ጤና መምሪያ....................................................... 17

ቅሬታና ይግባኝ ............................................................ 18

መግለጫዎች..................................................................24

# አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮችና መረጃዎች

## የአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥሮች

- ለሕይወትዎ አስጊ የሆነ ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥምዎት፡- 911 ብለው ይደውሉ ወይም በአቅራቢዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ። የአደጋ ጊዜ አገልግሎት ለማግኘት የባለስልጣን ፍቃድ አያስፈልግዎትም።
- ለመድሃኒት አጠቃቀም፥ ከቁማርተኝነት ጋር ለሚያያዝ ችግር፥ እና ለአእምሮ ጤና በ24-ሰዓት ውስጥ የአደጋ ጊዜ አገልግሎትና ምክር ከፈለጉ ወደሚከተለው የዋሽንግተን የማገገሚያ እርዳታ ስልክ ቁጥር በነፃ ይደውሉ፥ ንግግሩ በምስጢር ነው የሚያዘው፡- ወደ 1-866-789-1511, TTY 1-206-461-3219 ይደውሉ ወይም ወደዚህ ድረገፅ ይግቡ፡- www.waRecoveryHelpLine.org
- በአከባቢዎ ስለሚገኝ የአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥር ማግኘት ከፈለጉ ወደሚከተለው ድረገፅ ይግቡ፡- https://www.dshs.wa.gov/sites/default/files/BHSIA/dbh/BHO/BHO_Contacts_For_Services.pdf

## የዋሽንግተን ግዛት የፀባይ ጤናና ማገገሚያ ክፍል

የፀባይ ጤና አገልግሎት የሚመለከት መረጃ ለማግኘትና ማንን ማነጋገር እንዳለብዎ ለማወቅ ከፈለጉ የሚከተለውን ይጠቀሙ (ይህ ከክላርክና ስካማኒያ ውጭ ላሉት የሚሆን ነው)

- የፀባይ ጤና ጥቅሞችን የሚገልፅ መፅሐፍ በተለያዩ ቋንቋዎች ለማግኘት፡- https://www.dshs.wa.gov/bha/division-behavioral-health-and-recovery/behavioral-health-benefits-book
- በአከባቢዎ ስለሚገኘው አገልግሎት ለማወቅ፡- www.dshs.wa.gov/BHOcontacts
- በመንግስት ስለሚደጎመው አገልግሎት ለማወቅ፡- 1-360-725-3700, 1-800- 446-0259 ወይም www.dshs.wa.gov/bha/division-behavioral-health-and-recovery

## የዋሽንግተን ግዛት የጤና እንክብካቤ ባለስልጣን (HCA)

በመንግስት ስለሚደጎሙ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ የእንክብካቤ ፕላኖች፣ ሌሎች የአእምሮአዊ ጤና ጥቅሞች፣ እና የትራንስፖርት መረጃዎችን ለማግኘት:- ወደ 1-800-562-3022, TDD/ TTY ይደውሉ፤ 1-800-848-5429 ወይም 711 (መስማት ለተሳናቸው ወይም የመናገር ችግር ላለባቸው ብቻ)። በተጨማሪ askmedicaid@hca.wa.gov በዚህ ኢ-ሜይል ወይም ይህን www.hca.wa.gov/ ይጎብኙ።

## የዋሽንግተን ግዛት የእርጅናና የረዥም ጊዜ ድጋፍ አስተዳደር (ALTSA)

የረዥም ጊዜ የፀባይ ጤና አገልግሎት በተመለከተ መረጃ ከፈለጉ:-

- 1-800-422-3263. ቅሬታዎች/የምስጢር የቅሬታ ፅሕፈት ቤቶች:- 1-800-562-6028. www.dshs.wa.gov/altsa

## የዋሽንግተን ግዛት አስተዳደራዊ (ፍትሃዊ) መሰማት ፅ/ቤት

- 1-800-583-8271. www.oah.wa.gov.
  PO Box 42489, Olympia 98504

## የአመሪካ የሲቪል መብቶች ፅሕፈት ቤት

- www.hhs.gov/ocr

## ማጭበርበርን ወይም ያለ አግባብ መጠቀምን እንዴት ሪፖርት እንደሚደረግ መረጃ

Medicaid ማጭበርበሪያ ቁጥር 360-586-8888

ስለ Medicaid አስተዳደርአገልግሎቶ ጥያቄዎች እባኮ የጤና ክብካቤ ባለስልጣን የደንበኞች ህክምና ድጋፍ አገልግሎት መስመርን(MACSC) 360-562-3022 ያግኙ።

## የአገልግሎቶች መረጃ

### የፀባይ ጤና አገልግሎት ለማግኘት ብቁ የሆነው ማን ነው?

የሜዲክኤድ ተጠቃሚዎች የሆኑ ሰዎች በሕክምናው ዘርፍ አስፈላጊ የሆነ የፀባይ ጤና አገልግሎት በነፃ ማግኘት ይችላሉ።

በማሕበረሰቡ ጋር ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር ውል በመግባት የፀባይ ጤና አገልግሎት እንሰጣለን። ለዚህ አገልግሎት ብቁ ለመሆን በእኛ ፕሮግራም የሚሸፈን በሽታ እና ክብካቤው በህክምና አፈላጊ ሊሆን ይገባል (የክብካቤ ማግኛ መስፈርቶችን ማሟላት ተብሎ ይታወቃል) የአእምሮ ጤና ወይም የአደንዛዥ እፅ በመጠቀም የሚመጡ የጤና መታወክ፥ የራሳቸው የሕክምና የብቃት መስፈርት አላቸው።

### እዚህ ቡክሌት ላይ የተገለፁትን አገልግሎቶች የሚሸፍነው ማን ነው?

የማሕበራዊና የጤና አገልግሎትቶች መምሪያ(DSHS) በመንግስት የሚደጎሙትን የባህሪ ጤና ስርዓቶችን የሚቆጣጠር ሲሆን የፀባይ ጤና አገልግሎት ለመስጠት ከባህሪ ጤና ድርጅቶች ወይም BHO ጋር ውል ይገባል። እንያንዳንዱ የፀባይ ጤና ድርጅት BHO በአንድ ወይ ሁለት ካውንቲ የተመሰረቱ ናቸው። የሜዲክኤድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከሆኑት የክላርክና ስካማኒይ ካውንቲ ኗሪዎች በስተቀር ማንኛውንም ሰው በፀባይ ጤና ድርጅት BHO መመዝገብ ይችላል።



## የፀባይ ጤና አገልግሎት ለማግኘት ማንን ነው ማነጋገር የሚኖርብኝ?

የባህሪ ጤና አገልግሎት ማግኘት እንዳለብዎት ካሰቡ፥ ወደ BHO ይደውሉ፥ ወይም ለቅበላ ግምገማ ወይም ምርመራ በበማህበረሰቦ ቀጠሮ ለማሲያዝ ወደ ተሸፈነ ኤጀንሲ ይሂዱ። እነዚህ ምርመራዎች ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚያስፈልግዎ ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተጨማሪ ስለ ባህሪ ጤና እና አገልግሎቱ ለማግኘት እንዴት እንደሚያመለክቱ መረጃ ይቀበላሉ ። አስፈላጊ ከሆነ፥ ይህ መረጃ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጪም እንዲገኝ ይደረጋል።

ከአደጋ ጊዜ አገልግሎት በስተቀር አብዛኞቹ የፀባይ ጤና አገልግሎት አከባቢዎ ላይ በሚገኘው የፀባይ ጤና ድርጅት BHO የተፈቀደ መሆን ይኖርበታል። ከፀባይ ጤና ድርጅት BHO ጋር ውል ወደ ፈፀመ ድርጅት በመሄድ የፀባይ ጤና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። ኤጀንሲ ለማግኘት በአከባቢዎ ያለ BHOን በ: www.dshs.wa.gov/BHOcontacts. ያግኙ

**በአከባቢዎ የሚገኝ የፀባይ ጤና ድርጅት BHO አድራሻ ለማወቅ ይህንን ድረገፅ ይጎብኙ፡- www.dshs.wa.gov/BHOcontacts**

## የብቁነት ማረጋገጫ ወይም ምርመራ በሚያደርጉበት ወቅት ምን ይሆናል?

የፀባይ ጤና አገልግሎት ባለሞያ የሆነ ሰው ከእርስዎ ጋር ተገናኝቶ ምን ዓይነት ሕክምና እንደሚያስፈልግዎ እንዲሁም የሁኔታዎ ደረጃ በፀባይ ጤና ድርጅት BHO የሚሰጥ አገልግሎት የሚይስፈልገው እንደሆን ይመረምራል። ይህንን ለመወሰን ወደ ባለሞያው በተደጋጋሚ መመላለስ ሊያስፈልገው ይችላል።

የፀባይ ጤና አገልግሎት ባለሞያው ስለ ጥንካሬዎና የሚያስፈልግዎ ነገሮች ሊያወያይዎት ይችላል። ግብዎን የሚመለከት ጥያቄዎችን ሊጠይቅዎት ይችላል። ስለ ታሪክዎ እና ባህልዎ ሊጠይቅዎት ይችላል። ስለ አእምሮ ጤናዎ እና አደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም፥ እንዲሁም ስለ ሌሎች የሕክምና ጉዳዮች እና ስለ እርሶ ጠቃሚ ጥያቄዎችን ሊጠይቅዎት ይችላል።

የባህሪ የጤና ሁኔታ አለቦ ቶብሎ ከተወሰነ እና አገልግሎተች ሁኔታውን የሚያሻሽሉ፤የሚያረጋጉ፤ሁኔታዎ ከመባባስ የሚጠብቁ ከሆነ፤ አገልግሎት ሰጪው የህክምና አማራጮችን ከእርሶ ጋ ይወያያል፡ አገልግሎቶች ካልተፈቀዱ ፤በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት አሎት:: እባኮ በገፅ 21 ላይ “ ይግባኝ እንዴት እከፍታለሁ “ በሚለው ክፍል ውስጥ ይግባኝ እንዴት እንደሚቅርብ ይመልከቱ::

## በ Medicaid ምን ተጨማሪ የአዕምሮ ጤና ክብካቤ ይሸፈናል?

ለ BHO አገልግሎቶች የክብካቤ ደረጃዎች መድረሻን የማያሟሉ ከሆነ፤ በጤና ክብካቤ በለ ስልጣን(HCA). ለሚሰጡ ለዝቅተኛ ደረጃ አገልግሎት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የአእ ምሮ ጤና አገልግሎትን በተመለከተ Medicaid የሚመራ ክብካቤ እቅዶን በቀጥታ ያነ ጋግሩ። በጤና ክብካቤ ባለስልጣን ጥቅሞች ውስጥ አደንዛዥ እፅ በመፀቀም ለሚፈጠር የጤና መዛባት ህክምና የለም፡፡

በ Medicaid የሚመራ ክብካቤ እቅድ ውስጥ ካልተመዘገቡ በሽተኞችን ተቀብሎ በነፃ የአዕምሮ ጤና አገልግሎት ለሚሰጥ በ1-800-562-3022 ይደውሉ ወይም http://www.hca.wa.gov/medicaid/Pages/index.aspx.

## ለማንኛውም አገልግሎት መክፈል ይኖርብኛል?

በፀባይ ጤና ድርጅት BHO ውል ውስጥ ያልገባ የፀባይ ጤና አገልግሎት ሰጪ ጋር ከሄዱ ለአገልግሎቱ መክፈል ሊኖርብዎት ይችላል። በሜዲክኤድ የማይሸፈን አገልግሎት ከጠየቁ፥ ወይም ጥያቄው ሕክምና የማያስፈልገው ከሆነ መክፈል ሊኖርብዎት ይችላል። ስለ አገልግሎት ሰጪው ወይም ስለ አገልግሎቱ እርግጠኛ ካልሆኑ የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ይጠይቁ።

## እንድከፍል ከተጠየቅኩስ?

ፍቃድ የሌላቸው አገልግሎቶች ከተጠቀሙ ወይም ፍቃድ ወደሌለው አገልግሎት ሰጪ ካልሄዱ በስተቀር፥ በሜዲክኤድ የሚሸፈኑ አገልግሎቶችን በተመለከተ መክፈል አይኖርብዎትም።

እንዲከፍሉ ከተጠየቁ፥ ክፍያውን እንዲፈፅሙ የጠየቅዎትን ባለስልጣን ለማግኘት ይሞክሩ። በሜዲክኤድ የሚሸፈንልዎት መሆንዎና ክፍያውን እንዲፈፅሙ የተጠየቁበትን ምክንያት ይጠይቁ።

ይህ ችግሩን ካልፈታው የፀባይ ጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪውን፥ የፀባይ ጤና ድርጅት BHO፥ ወይም በምስጢር ቅሬታ ሰሚ አካሉን እርዳታ ለማግኘት ይሞክሩ።

## በምስጢር ቅሬታ ሰሚ አካል ምንድን ነው?

እንባ ጠባቂ ከእርሶ እና BHO ጋር ቅሬታዎች ፤ይግባኞች እና አስተዳደራዊ (ፍትሃዊ) መሰማቶች ለማቅረብ የሚሰራ ሰው ነው፡፡ በአከባቢዎ የሚገኝ በምስጢር ቅሬታ ሰሚ አካሉ አድራሻ በፀባይ ጤና ድርጅት BHO የአድራሻ ዝርዝር ውስጥ ይገኛል፦ www.dshs.wa.gov/BHOcontacts. ወደ 1-800-446-0259 መደወልም ይችላሉ። ይህ በነፃ የሚሰጥ አገልግሎት ነው።

## ወደ ሕክምና ለመሄድ ትራንስፖርት የሚያስፈልገኝ ከሆነስ?

በአብዛኛው ሁኔታ ሜዲክኤድ ለጤና አገልግሎት ቀጠሮ የሚወጣውን የትራንስፖርቱን ወጪ ይሸፍናል። ትራንስፖርት ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ በ 1-800-562-3022 የእርሶ BHO ጋር ይደውሉ፡፡

## በድንገተኛ ክፍል ውስጥ እንክብካቤ የማገኘው እንዴት ነው?

ከፀባይ ጋር የሚያያዝ ወድያውኑ ሕክምና የሚያስፈልገው ድንገተኛ ወይም ከባድ ችግር ሲያጋጥምዎት፥ የፀባይ ጤና ድንገተኛ አገልግሎት ሊረዳዎት ይችላል። ለሂወቶ አስጊ ድንገተኛ ነገር ካጋጠምዎት 911 ብለው ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ። እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት የቅበላ ግምገማ፤ምርመራ ወይ የቅድሚያ ፍቃድ አያስፈልግዎትም፤ አገልግሎቱም በነፃ ነው። ለድንገተኛ ክብካቤ ማንኛውም ሆስፒታል ወይም ሌላ ቦታን የመጠቀም መብት አሎት፡፡

## ለባህሪ ጤና ክብካቤ ሆስፒታል መሄድ ብፈልግስ?

ለባህሪ የጤና ህክምና ሆስፒታል መግባት ያስፈልገኛል ብለው ካሰቡ ፤የባህሪ ጤና ክብካቤ ሰጪዎን ያነጋግሩ ወይም የአስቸኳይ የአደጋ ጥሪ መስመሩን ወይም በቅርብ ወደሚገኝ የድንገተኛ የህክምና ክፍል ይሂዱ፡፡ በሆስፒታል የሚሰጥ አገልግሎትን የተመለከተ ወጪ ለሜዲክኤድ ተመዝጋቢዎች ይሸፈንላቸዋል። ይሁን እንጂ አስቀድሞ በፀባይ ጤና ድርጅት BHO የተፈቀደለት ሊሆን ይገባል፥ አለበለዚያ ለአገልግሎቶቹ እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ።ሆስፒታል ውስጥ እንክብካቤ ከተደረገልዎት፥ ሌላ አደጋ እንዳያጋጥም ከተከላከሉና በማገገሙ ላይ ከረዱ በኋላ ነው።

## ምን ምን አገልግሎቶች አሉ?



እርስዎ፥ የፀባይ ጤና አገልግሎት ሰጪዎ እና ሌሎች ሊጋብዟቸው የሚፈልጉ ሰዎች፥ ለእርስዎ ዕቅድ ሊያወጡ ይችላሉ። የእርስዎ “የግል አገልግሎት/ሕክምና ዕቅድ” በእርስዎ፥ በቤተሰብዎ፥ እና በማሕበረሰቡ ጥንካሬ ላይ የሚመሰረት እና ዕድሜዎትን፥ ባህልዎትን፥ እንዲሁም እምነትዎትን የሚያከብር ነው።

የዕቅድዎ አካል ከሆኑ የሚከተሉትን አገልግሎትቶችን የማግኘት መብት አለዎት፡-

### መድሃኒት የሚያስፈልገው ሕመም

- **ምርመራ** – በጤና አገልግሎት ሰጪ የሚደረግ ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚያስፈልግዎ ለመወሰን የሚረዳ ቃለ መጠይቅ
- **አጭር ጣልቃ ገብነት እና የሕክምና ሪፈራል** – በጊዜ የሚወሰን፥ የችግር አጠቃቀም ለመቀነስ
- **ከአልባሌ ሱሶች ማላቀቂያ (ሰውነትን ማጽዳት)** – ቀስ በቀስ እርስዎን በማይጎዳ መልኩ የአልኮልና የአደንዛዥ ዕፅ መጠቀምዎን እንዲቀንሱ የሚረዳ (በሆስፒታል የሚሰጥ ሕክምና በሜዲክኤድ ድጎማ የሚሸፈን ይሆናል)
- **አልጋ ሳይዙ የሚሰጥ ሕክምና** - በማሕበረሰብዎ የሚደረግ ግለሰቦች እና ቡድኖች የሚያደርጉት የምክክር ክፍለ ጊዜ
- **ከፍተኛ ደረጃ ያለው አልጋ ሳይዙ የሚሰጥ ሕክምና** – ግለሰቦች እና ቡድኖች ይበልጥ በተደጋጋሚ የሚያደርጉት የምክክር ክፍለ ጊዜ
- **መኖሪያ ቤቶች የሚሰጥ ሕክምና** – በ24 ሰዓት ቁጥጥር በሚደረግበት ቦታ የሚሰጥ በግለሰብ እና የቡድን ደረጃ የሚሰጥ የምክር አገልግሎት ያቀፈ አጠቃላይ መርሀ ግብር
- **በአደንዛዥ ዕፅ ምትክ የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት** – አልጋ ሳይዙ የሚሰጥ ምርመራ እና የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኞች ለሆኑ የሚሰጥ ሕክምና። ፍቃድ የተሰጣቸው መድሃኒቶችና የምክር አገልግሎት ያካትታል
- **የእያንዳንዱ ጉዳይ ስራ ማስኬድ** – የሕክምና፥ የማሕበራዊ፥ የትምህርት፥ እና ሌሎች አገልግሎቶች ለማግኘት የሚረዳ

## የአእምሮ ጤና

- **የማስገቢያ ምርመራ** - የሚያስፈልግዎትን ነገሮችና ግብዎትን ለይቶ ማወቅና እርስዎንና የአእምሮ ጤና እንክብካቤ ሰጪዎን የሕክምና ዕቅድ ለይቶ በመወሰን ረገድ መርዳት
- **የአደጋ ጊዜ አገልግሎት** – የሚያስፈልግዎትን ነገር በሚመችዎት አከባቢ ሆነው ይበልጥ መሻሻል እንዲያሳዩ የሚረዳዎት የ24 ሰዓት አገልግሎት። ከዚህ አገልግሎት በፊት የማስገቢያ ምርመራ ማድረግ አያስፈልግዎትም
- **በግለሰብ የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት** - የአገልግሎት ዕቅድ ግብዎ እንዲያሳኩ የሚረዳዎት የምክር እና/ወይም ሌሎች አገልግሎቶች
- **የሕክምና ስራ ማስኬጃ** - ፍቃድ ያላቸው ሰራተኞች መድሃኒት የሚያዙበት እና የመድሃኒቶቹ የጎንዮሽ ችግር የሚያስረዱበት
- **የመድሃኒት ቁጥጥር** - የሚወስዱት መድሃኒት እንዴት እየሰራ እንዳለ የሚረጋገጥበት እና እንዴት በትክክል መውሰድ እንዳለብዎት እንዲያውቁ የሚረዳዎት አገልግሎት
- **የቡድን ሕክምና አገልግሎት** – ተመሳሳይ ችግር ከሚያጋጥማቸው ሰዎች ጋር የሚደረግ የምክር አገልግሎት
- **የእኩዮች ድጋፍ** – የህዝቡ የአእምሮ ጤና ስርዓት ለይቶ ለማወቅ የሚረዳና የሚደግፍ፥ እንዲሁም የማገገሚያ ግብኞ ላይ እንዲደርሱ የሚረዳ፥ ይህም የሚደረገው በሰለጠነ ሰው ወይም ከአዕምሮ ጤና ችግር በማገገም ላይ ያለ ወላጅ ነው።
- **አጭር ጣልቃ ገብነት እና ሕክምና** - በአንድ ችግር ላይ ያተኮረ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ የምክር አገልግሎት
- **የቤተሰብ ሕክምና** - ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር፤ ለውጤታማ ስልት እና ችግር መፍታት የሚረዳ በቤተሰብ ላይ ያተኮረ የምክር አገልግሎት።
- **በከፍተኛ ሁኔታ የሚሰጥ ሕክምና** - የግልዎ ዕቅድ ላይ እንዲደርሱ የሚያስችል የአእምሮ ጤና አገልግሎት በሚሰጡ ቡድን አማካኝነት የሚሰጥ አገልግሎት
- **የሕክምና የስነ አእምሮ ትምህርት** - ስለ አእምሮ ጤና ሁኔታ፥ ስለ ሕክምና ምርጫ፥ ስለ መድሃኒትና ማገገም፥ እንዲሁም ስለ ደጋፊዎች እና/ወይም ደጋፊ አገልግሎቶች የሚገልፅ ትምህርት

- **የቀን ድጋፍ** - በግልዎ በሚኖሩበት ወቅት ስለሚያስፈልግዎት ክህሎት እንዲማሩ ወይም እንዲያውቁ የሚረዳ ከፍተኛ መርሀ ግብር

- **የጤና ሁኔታ ምዘናና የህክምና ክትትል ወይም የማህበረሰብ ህክምና** — በህክምና የሚያስፈልግ ለውስጥ ታካሚ የሚደረግ ችግር ክብካቤ። ከዚህ አገልግሎት በፊት የማስገቢያ ምርመራ ማድረግ አያስፈልግዎትም

- **የማረጋጊያ አገልግሎቶች** — በሆስፒታል እንዳይቆዩ በቤትዎ ወይም ቤትዎን በሚ መስል አካባቢ የሚሰጥ አገልግሎት። ከዚህ አገልግሎት በፊት የማስገቢያ ምርመራ ማድረግ አያስፈልግዎትም

- **የተሐድሶ ጉዳይ ስራ ማስኬጃ** - በሆስፒታል አልጋ ይዘው የሚታከሙትንና ከሆስፒ ታል ውጭ የሚታከሙትን የአእምሮ ጤና አገልግሎት ለማስተባበር የሚረዳ። ይህ የማስገቢያ ግምገማው ክፍል ሊሆን ይችላል

- **የመኖርያ ቤት አገልግሎት** - የሚኖሩበት አከባቢ በቡድን ዓይነት ከሆነ የሚሰጥ አገልግሎት

- **ለልዩ ህዝብ የሚደረግ ግምገማ** – ከህፃናት፥ ከአዋቂዎች እና ከተለያየ ባህል ከመጡ ሰዎች ጋር የሚሰራ ባለሞያ የሚሰጠው የሕክምና ዕቅድ እርዳታ

- **የሳይኮሎጂ ግምገማ** – ሕመምን ለይቶ ለማወቅ፥ ለመገምገም እና ለሕክምና ዕቅድ የሚረዳ የምርመራ ዓይነት

## በሞራል ወይም በሃይማኖት ምክንያቶች ላይ የባህሪ ጤና ክብካቤ ሰጪ አገልግሎት አለመስጠት ይችላልን?

የባህሪ ጤና ክብካቤ አቅራቢ አንዳንድ አገልግሎቶችን ከሞራል ወይም ከሃይማኖት ምክንያ ቶች የተነሳ ላያቀርብ፤ክፍያ ላይተካ ወይም ላይሸፍን ይችላል፡፡ አቅራቢው የማይሰጡትን የአገልግሎቶች ዝርዝር እና እነዚህን አገልግሎቶች ከሌላ አቅራቢ ለማግኘት መንን መነጋር እንዳለቦት መረጃ የግድ ሊያቀርብሎ ይገባል፡፡

### የፀባይ ጤና እንክብካቤ የሚሰጠኝን አካል መምረጥ እችላለሁ?

BHO ውስጥ የተካተተ የባህሪ ጤና እንክብካቤ የሚሰጥ አገልግሎት ሰጪ መምረጥ ይችላሉ። የፀባይ ጤና ድርጅት BHO በአከባቢዎ በሚገኙትን የአገልግሎት ሰጪዎችን ስም፥ አድራሻ፥ ስልክ ቁጥር፥ እና ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጭ የሚነገሩ ቋንቋዎችን ዝርዝር ይሰጥዎታል። አገልግሎት ሰጪ ካልመረጡ፥ አንድ ይመደብልዎታል። በማንኛውም ጊዜ አገልግሎት ሰጪውን የመቀየር መብት አለዎት።

### የማገገሚያ ድጋፍ ቡድን ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

ወደ የዋሽንግተን የማገገሚያ እርዳታ ማዕከል እና የምስጢር ሪፈራሎች በነፃ ይደውሉ:- 1-866-789-1511.

### በሜዲክኤድ የሚሸፈን የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

የመጀመሪያ ክብካቤ የሚሰጠ ከሌለ ወይም የመጀመሪያ ክብካቤ የሚሠጠን ለመቀየር ከፈለጉ ወደ www.hca.wa.gov/free-or-low-cost-health-care/apple-health-medicaid-coverage ወይም በእርሶ አከባቢ የሚገኝን ለመምረጥ እንዲረዳዎ 1-800-562-3022 ላይ ይደውሉ:: የፀባይ ጤና አገልግሎት ሰጪዎ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊረዳዎት ይችላል። የመጀመሪያ ክብካቤ ሃኪሞን በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ::

ድጎማዎትን በተመለከተ ለማወቅ ወደ ሕክምና ቀጠሮ ሲሄዱ የሕክምና ካርድዎን መያዝዎ አይርሱ።

አዲስ ለተወለዱና እስከ 21 ዓመት ላሉት ልጆት፥ የመጀመሪያና በየጊዜው የሚደረግ የሕክምና ምርመራ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። የጤና ምርመራ ማድረግ፥ ልጅዎ ሌላ ከጤናው ጋር የሚያያዝ እርዳታ የሚያስፈልገው እንደሆን ለማወቅ ይረዳል። ከዚያ ቀጥሎ ዶክተሩ በሌላ ቦታ ሄደው ሕክምናውን እንዲከታተሉ ሪፈራል ሊፅፍልዎት ይችላል።

# የህፃናት የመጀመሪያና በየጊዜው
# የሚደረግ የሕክምና ምርመራ ምንድን ነው?

## ለህፃናት የሚሆን የመጀመሪያና በየጊዜው የሚደረግ የሕክምና ምርመራ ምንድን ነው?

ለህፃናት የሚሆን የመጀመሪያና በየጊዜው የሚደረግ የሕክምና ምርመራ (EPSDT) ከልደት እስከ 21 ዓመት ላሉት በሜዲክኤድ ለሚሸፈንላቸው ህፃናት የሚሆን የጤና ፕሮ ግራም ነው፥ ይህም የማደጎ ልጆችን የሚጨምር ሲሆን ከሌሎች አገልግሎቶችም ጋር የሚ ያገናኝ ነው። በ EPSDT ህፃናት መደበኛ የጤነኛ ህፃን ምርመራዎችን ሊያገኙ ይችላሉ: : ልጅዎ በሕክምናው አማካኝነት ለታወቀ ሕመም የሚሆን የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት ካስፈለገው፥ ሜዲክኤድ አስፈላጊ ለሆኑ የሕክምና ክትትሎች የሚወጣውን ወጪ ይሸፍ ናል። የመጀመሪያና በየጊዜው የሚደረግ የሕክምና ምርመራ (EPSDT) ወቅት ልጅዎ በየ ፀባይ ጤና ድርጅት BHO ወይም በልጅዎ የጤና ዕቅድ አማካኝነት የፀባይ ጤና ምርመራ እንዲያደርግ ሊጠየቅ ይችላል። የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ውስጥ የማስገቢያ ምርመራ ይደረግልዎታል።

## ልጆች መቼ ነው ምርመራውን ማድረግ የሚኖርባቸው?

**መግለጫ፡-** ህፃናት የመጀመሪያ የጤና ምርመራቸውን የህክምና አገልግሎቶች ካርድ እንደተወሰደ ወዲያውኑ ማግኘት አለባቸው፡፡

- በመወለድ እና 1 ዓመትመሃል ህፃናት አምስትምርመራዎች ማድረግአለባቸው፡፡
- በአንድ እና ሶስት ዓመት ልዳታቸው መሃል ህፃናት ምርመራ ማድረግ አለባቸው፡፡
- እድሜያቸው ከሶስት እስከ ስድስት የሆኑ ህፃናት በዓመት አንዴ ምርመራ ማግኘት አለባቸው፡፡.
- ከሰባት እስከ 20 ዓመት የሆኑ ልጆች በሁለት ዓመት አንዴ ምርምራ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

- ሁሉም ተመካሪ የልጅነት ጊዜ ክትባቶች ይካተታሉ።
- እንደ ህፃኑ እድሜ፤የመስማት እና የመስማት ምርመራ፤አንዳንድ የቤተ ሙከራ ምርመ ራ፤የእድገት እና የባህሪ ማጣራቶች ይካተታሉ (ለምሳሌ የኦቲዝም ማጣራት)።
- ችግር ከተገኘ ፤የባህሪ ችግርን ጨምሮ ፤የክትትል ምርመራዎች እና ህክምናም ይሸፈናሉ።
- ካስፈለገ ለባህሪ ጤና ፍተሳ ምሪት በማንኛውም በነዚህ ቀጠሮዎች ሊሰጥ ይችላል። ልጅዎ ከፀባይ ጤና ባለሞያ ጋር ከተገናኘ በኋላ፥ ከዋነኛ አገልግሎት ሰጪው ጋር በመሆን አጠቃላይ የጤና እንክብካቤ ዕቅድ ሊያወጡ ይችላሉ።

**መግለጫ፦** ልጅ ሊኖርበት የሚችል ማንኛውንም አፋጣኝ የህክምና፤የጥርስ ወይም አስ ቸኳይ የጤና ፍላጎት ለመለየት በማደጎ ክብካቤ ውስጥ ያሉ ልጆችም የመጀመሪያ የጤና ግምገማ ይቀበላሉ። የጉዲፈቻ ወላጆች እና የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ማወቅ ያለባቸው ማንኛውም ተጨማሪ የጤና ሁኔታ ጋር

በ EPSDT ስር የሚደረጉ አንዳንድ የጥርስ፤የአዓን እና የጆሮ ማጠራቶችንም Medicaid በተጨማሪ ይሸፍናል።

## እኔ ወይም ልጄ የጥርስ ሐኪም ካስፈለገንስ?

በሜዲክኤድ ለተመዘገቡ በተወሰነ ደረጃ የጥርስ ሕክምና ወጪ ይሸፈንላቸዋል። የጥርስ ሐኪም ለማግኘት፥ በአከባቢዎ ወደሚገኝ የጥርስ ሐኪሞች ማህበር ይደውሉ። በየሎው ፔጅስ (የስልክ ቁጥር ማውጫ) ላይ “የጥርስ ሐኪሞት” በሚለው ስር ይገኛል ወይም ወደ 1-800-562-3022 ይደውሉ።

ብቁ ህፃናት ያለ ሃኪም ምሪት ወደ ጥርስ አቅራቢ መሄድ ይችላሉ። ለጎልማሳ Medicaid ተመዝጋቢዎች የተወሰነ የጥርስ ሽፋን አለ። የጥርስ ሃኪም ለማግ ኘት ለ Apple Health/Medicaid እርዳታ መስመር በ1-800-562-3022 ላይ ይደውሉ ወይም ይህን ማገናኛ ይከተሉ https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider/

## በማሕበረሰቡ ውስጥ በመንግስት ድጎማ የሚደረግለት የፀባይ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንደመሆኔ መጠን መብቶቼ ምንድን ናቸው?

እርስዎ የሚከተሉት መብት አልዎት፡

- የጠየቁትን መረጃና በሜዲክኤድ የሚሸፈኑትን አገልግሎት የማግኘነት መብት
- በአክብሮት የመያዝ፥ ክብርዎትን የመጠበቅ፥ እና የግል መረጃዎትን በምስጢር የመያዝ መብት
- ስለሚያገኙት እንክብካቤ ውሳኔ የማድረግ መብት፥ እንዲሁም አንድ ዓይነት ሕክምና ያለመቀበል መብት
- ያለመታገድና ያለመገለል መብት
- የፀባይ ጤና እንክብካቤ የበሽተኞች መብት የሚገልፅ ሰነድ ቅጅ የማግኘት መብት
- የሕክምና መረጃዎትን የሚገልፅ ሰነድ ቅጅ የማግኘት እና ሰነዱ እንዲሻሻል ወይም እንዲታረም የመጠየቅ መብት
- ማግኘት ስለሚቻለው የፀባይ ጤና ጥቅማ ጥቅሞችን የሚመለከት መረጃ የማግኘው መብት
- በተሰጦት አገልግሎት ካረኩ ቅሬታ፤ይግባኝ ወይም አስተዳደራዊ(ፍትሃዊ) መሰማት ያቅርቡ፡፡
- የአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥሮች ዝርዝር የማግኘት መብት



- አገልግሎት ሰጪውን ወይም የጉዳይ ስራ አስኪያጁን በማንኛውም ጊዜ የመቀየር እና ቅሬታ ወይም ይግባኝ ሲያቀርቡ ወይም ጉዳይዎ እንዲታይልዎ ሲጠይቁ በምስጢር ጉዳይ የሚሰማን አካል አገልግሎት የማግኘት መብት
- ከመሰናክል ነፃ በሆነ አከባቢ አገልግሎት የማግኘት መብት
- በየዓመቱ ወይም በጠየቁበት ወቅት የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ስም፥ አድራሻ፥ ስልክ ቁጥር፥ እና ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጪ የትኞቹን ቋንቋዎች መጠቀም እንደሚቻል የሚገልፅ መረጃ የማግኘት መብት
- የሚፈልጉትን አገልግሎት መጠን እና የጊዜ ርዝማኔ የማወቅ መብት
- አገልግሎቶች ከተከለከሉ፤ከተገደቡ፤ከተቀነሱ፤ከታገዱ ወይም ከተቋረጡ፤ክፍያ ከተከለከለ ወይም ከእቅዱ ጋር ካልተስማሙ ከ BHO ላይ የፅሁፍ ጎጂ ጥቅም ውሳኔ ማሳወቂያ ይቀበሉ፡፡
- የፀባይ ጤና ድርጅት BHO መዋቅር የስራ ሂደት በተመከለተ መረጃ የማግኘት መብት
- የድንገተኛ ጊዜ ወይም አጣዳፊ እንክብካቤ ወይም የአደጋ ጊዜ አገልግሎት የማግኘት መብት
- ድኅረ-መረጋጋት አገልግሎቶችን ይቀበሉ
- ድንገተኛው ጉዳይ ከተረጋጋ በኃላ ከድንገተኛ ህክምና ጋር የተያያዙ ድኅረ-መረጋጋት አገልግሎቶችን ይቀበሉ፡፡
- ለዕድሜዎ እና ባህልዎ የሚመጥን አገልግሎት የማግኘት መብት
- ብቃት ያለው ተርጓሚና የተተረጐመ ፅሑፍ በነጻ የማግኘት መብት
- በመረጡት ቋንቋና ፎርማት መሰረት የጠየቁትን መረጃና እርዳታ የማግኘት መብት
- ሊገኙ የሚችሉትን የሕክምና አማራጮች በሚገባ እንዲገለፅልዎት የመጠየቅ መብት
- ማንኛውንም የቀረበልዎት ዓይነት ሕክምና ያለመቀበል መብት
- እርስዎ ላይ አድልዎ የማያደርስ እንክብካቤ የማግኘት መብት (ለምሳሌ፦ በዕድሜ፥ በዘር፥ በበሽታ ዓይነት)

- ለማንኛውም ዓይነት የፆታ ጉዳት እና ትንኮሳ ያለመጋለጥ መብት
- ስለሁሉም የታዘዘልዎት መድሃኒት እና የጎንዮሽ ጉዳቱን የሚገልፅ መረጃ የማግኘት መብት
- የአዕምሮ ጤና ክብካቤ ምረጫዎትን እና ፍላጎቶትን የሚገልፅ የህክምና ቅደመ መመ ሪያዎች እንዴት መስራት እና መጠቀም እንደሚገባዎ መረጃ ይቀበሉ፡፡
- ለሕክምና አስፈላጊ የሆነ ጥራት ያለው አገልግሎት የማግኘት መብት
- ከአቅራቢዎ ጋር ካልተስማሙ ሁለተኛ አስተያየት ያለ ምንም ወጪ ከብቁ ባለሙያ ይቀበሉ፡፡ ለራሶ እና ለልጆ (ልጆ ከ13 ዓመት በታች ከሆነ) አቅራቢ ይምረጡ፡፡
- የጤና ሰነድዎ ቅጂ የመጠየቅና የማግኘት መብት። የኮፒ ማድረጊያ ሒሳብ ሊነገርዎ ይችላል
- ቅሬታ፤ይግባኝ ወይም አስተዳደራዊ(ፍትሃዊ) መሰማት አቤቱታን ጨምሮ የእንባ ጠባቂ አገልግሎቶችን ይቀበሉ፡፡

ለተጨማሪ መረጃ የሲቪል መብቶች ፅ/ቤትን በ www.hhs.gov/ocr / apps.leg.wa.gov/wac/default.aspx?cite=388-877-0680 ላይ ያግኙ ፡፡

## የደንበኛ እርካታ ጥናት ይካሄዳል?

ቢያንስ በዓመት አንዴ በፍቃደኝነት የሚደረግ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት፥ አንዲ ቅጂ ወደ እርስዎ ይላካል፥ ይህም እርስዎ እና ቤተሰብዎ ስለሚያገኙት አገልግሎት ምን እን ደሚሰማዎት ለማወቅ ያስችለናል። ይህ ጥናት ከተላከልዎ፥ እባክዎትን ጊዜ ሰጥተው መልስ ይስጡበት። የሚሰጡት አስተያየት የሚያገኙትን የእንክብካቤ ጥራይ ሊያሻሽለው ይችላል። ማንኛውንም የሚሰጡት መረጃ በምስጢር ይያዛል።

# የአእምሮ ጤና መምሪያ ፅሑፍ

## የአእምሮ ጤና መምሪያ ፅሑፍ ምንድን ነው?

የአእምሮ ጤና መምሪያ ፅሑፍ በአደጋ ጊዜ ወይም ከባድ ችግር በሚያጋጥመትና ሆስፒታል በሚገቡበት ወቅት ምን እንዲደረግ እንደሚፈልጉ የሚገልፅ ሰነድ ነው። ምን ዓይነት ሕክምና እንደሚፈልጉና እንደማይፈልጉ ለሌሎች ሰዎች ይገልፅላቸዋል። ውሳኔ እንዲያደር ግልዎ የመረጡትን ሰው መረጃ የያዘ ጭምር ነው።

የሕክምና መምሪያ ፅሑፍ ካለዎት፥ ለአእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጪ ይስጡት፥ እንዲህ ካደረጉ የእርስዎን ፍላጎት ማወቅ ይቻላል።

## የሕክምና መምሪያ ፅሑፍ መሙላት የምችለው እንዴት ነው?

የቅድሚያ መመሪያ ቅፁን እና ስለ መመሪያዎች ተጨማሪ መረጃ www.dshs.wa.gov/bha/division-behavioral-health-and-recovery/mental-health-advance-directives ላይ ወይም ለሸመሰች ሸርክናዎች ፅ/ቤት በ 1-800-446-0259 ይደውሉ። ቅፁን የእርሶ BHO የባህሪ ጤና ክብካቤ አቅራቢዎ ወይም የእርሶ እንባ ጠባቂ ሊሰጦት ይችላል።



# ቅሬታዎች/ይግባኞች/አስተዳደራዊ (ፍትሃዊ) መስማቶች

## በአገልግሎቱ ካልተደሰትኩ ምን ማድረግ አለብኝ?

በአገልግሎቶ ድስተኛ ካልሆኑ፤የሸማች መብቱን በመጥቀስ ራሶ ጉዳዩን ለመፍታት ሊሞክሩ ይችላሉ። ተጨማሪ እርዳታ ከፈለጉ ለ BHO ወይም አገልግሎቶን ለሚሰጠ ለባህሪ ጤና አቅራቢ ሊነግሩት ይችላሉ። እንደዚያ አድርገው መፍትሔ ካላገኙ፡-

- ቅሬታዎን በምስጢር ጉዳይ የሚሰማን አካል ጋር በመሄድ ይንገሩ። እንደ ምርጫዎ በአቅራቢዎ ወይም BHO ላይ ቅሬታ እንዲያቀርቡ ይረዶታል።
- ከ እራሶBHO እና/ወይም የጎጂ ጥቅም ውሳኔ ማስታቀቂያ በፅሁፍ ከተሰጠ ይግባኝ ያቅርቡ ።
- ይግባኞ እርሶን በሚያረካ መልኩ ካልተወሰነ አስተዳደራዊ(ፍትሃዊ) መስማት ይጠይቁ።

## ቅሬታ፥ የይግባኝ ጥይቄ፥ ወይም አስተዳደራዊ ጉዳይ መስማትን በተመለከተ ማን ሊረዳኝ ይችላል?

በምስጢር ጉዳይ የሚሰማን አካል፥ የፀባይ ጤና ድርጅት BHO፥ አገልግሎት የሚያገኙ በት የፀባይ ጤና አገልግሎት ሰጪ ወይም ሌላ ማንኛውም የመረጡት ሰው ከፀባይ ጤና አገልግሎት ጋር የሚያያዝ ማንኛውንም ጉዳይ እንዲፈቱ ሊረዳዎት ይችላል። ተርጓሚም ካስፈለገ ያለ ያለምንም ወጪ ይቀርባል።

## ቅሬታ ማቅረብ የምችለው እንዴት ነው?

የቅሬታ ማቅረቢያ ሂደት የሚከተለውን ይመስላል:-

1. ቅሬታዎን የባህሪ ጤና አገልግሎት ሰጪዎ ወይም BHO ጋር በአካል፥ በስልክ፥ ወይም በጽሑፍ ማቅረብ ይችላሉ። በምስጢር ጉዳይ የሚሰማን አካል፥ የፀባይ ጤና ድርጅትን በተመለከተ ለእርዳታ መጠየቅ ይችላሉ። ቅሬታዎን በጽሑፍ ካቀረቡ፥ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለብዎት:-
    - ስምዎ፥
    - አድራሻ፥
    - ያጋጠምዎትን ችግር፥
    - ችግሩን በተመለከተ ምን መደረግ ይኖርበታል ብለው እንደሚያስቡ፥
    - ፊርማዎትን እና የፈረሙበትን ቀን
2. አገልግሎት ሰጪው ወይም የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ቅሬታዎ እንደደረሳቸው፥ በአምስት የስራ ቀን ውስጥ ቅሬታዎ እንደደረሳቸው በጽሑፍ ያሳውቅዎታል።
3. ቅሬታዎ ከዚህ በፊት ጉዳዩ(ዮቹ) ላይ ባልነበሩ ሰዎች ይታያል። ቅሬታዎ ከፀባይ ጤና አያያዝ ጋር የሚያያዝ ከሆነ፥ ጉዳዩን ከሚመረምሩት ውስጥ የፀባይ ጤና እንክብካቤ ባለሞያ ይኖራል።
4. ውሳኔው በተደረገ በ90 ቀን ውስጥ ከድርጅቱ ደብዳቤ ይደርስዎታል። አቅራቢው ጋር ቅሬታ ከአቀረቡ እና በውሳኔው ድስተኛ ካልሆኑ፤ሁለተኛ ቅሬታ በእርሶ BHO ጋር ማቅረብ ይችላሉ።:  BHO ጋር መነሻ ቅሬታዎን በቀጥታ ማቅረብ ይችላሉ።:
5. የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ቅሬታዎ እንደደረሰው በአምስት ቀናት ውስጥ ያሳውቅዎ ታል።
6. የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ቅሬታዎን እና የአገልግሎት ሰጪውን ውሳኔ መርምሮ ውሳኔውን በ90 ቀናት ውስጥ በደብዳቤ ያሳውቅዎታል።

## ጎጂ ጥቅም ውሳኔ ምንድ ነው?

**1.** የተከለከለ ወይም በከፊል የተፈቀደ በ Medicaid የተሸፈነ አገልግሎት ጥያቄ

**2.** በ BHO ቀድሞ ፍቃድ የተሰጠው አገልግሎት መቀነስ፤መታገድ ወይም መቋረጥ

**3.** በBHO የአገልግሎት ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል መከልከል፡፡

**4.** በግዛቶች እንደተቀመጠው BHO ወይም አቅራው በወቅቱ አገልግሎት ለእርሶ መስጠት አለመቻል፡፡

**5.** በDSHS ደንቦች ውስጥ እንደተደነገገው ለቅሬታ እና ለይግባኝ በተቀመጠው የግዜ ገደብ ውስጥ BHO ውሳኔ አለመስጠቱ

አቅራቢዎ በሰጠው ህክምና አሰጣጥ ውሳኔ ካልተስማሙ፤ከአቅራቢዎ ጋር ልዩነቱን ለመፍታት ሊሞክሩ ይችላሉ ወይም ውሳኔው እንደ ጎጂ ጥቅም ውሳኔ እንዲታይ ለመጠየቅ BHOን ማነጋገር ይችላሉ፡፡

## የጎጂ ጥቅም ውሳኔ ማሳወቂያ ምንድ ነው?

የፀባይ ጤና ድርጅት BHO የሜዲክኤድ የፀባይ ጤና አገልግሎት አለመቀበሉን፥ ለጊዜው ማቋረጡን፥ መቀነሱን፥ ወይም ከነጭራሹ ማቋረጡን የሚገልጽ ደብዳቤ ነው። ይህ ደብዳቤ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ደብዳቤው የተፃፈበት ምክንያት።
- ለጎጂ ጥቅም ውሳነው ምክንያቱ::
- ይግባኝ፤የተፋጠነ ይግባኝ ወይም አስተዳደራዊ(ፍትሃዊ) መሰማት መብቶ
- አማራጭ የሚሆን ሁለተኛ አስተያየት የመያዝ መብትዎ
- በይግባኝ ሂደቱ ወቅት ቀጣይ አገልግሎቶች የማግኘት መብቶ::

## ይግባኝ ማቅረብ የምችለው እንዴት ነው?

ከ BHO ጎጂ ጥቅም ውሳኔ ከተቀበሉ እና በውሳኔው ካረኩ፤ሊከተሉአቸው የሚችሉ ደረጃዎች እና የእርሶ BHO ምላሽ የሚሰጥበት ሂደት እኙሁሎ

1. የፀባይ ጤና ድርጅትን BHO በአካል፥ በስክል፥ ወይም በጽሑፍ ይግባኝ እንደሚያቀ ርቡ ያሳውቁ። የእርምጃ ማስጠንቀቂያው ላይ ከተጠቀሰው ቀን ጀምረው በ60 ቀን ውስጥ የይግባኝ ጥያቄዎን ያቅርቡ። የይግባኝ ጥያቄዎ ላይ የሚከተሉትን ያካትቱ፡-
    - ስምዎ፥
    - አድራሻ፥
    - በጎጂ ጥቅም ውሳኔው ለምን አልተስማሙም እና
    - ፊርማዎ እና የፈረሙበት ቀን።

2. የጎጂ ጥቅም ውሳኔዎ ከቅባላ ምርመራ በኃላ አገልግሎች ከከለከሎት ማሳወቂያ የሚይ ዘው፡
    - አማራጭ የሚሆን ሁለተኛ አስተያየት የመያዝ መብትዎና እንዴት ይህንን ማግኘት እንደሚችሉ፥
    - በHCA አማካኝነት ወይም በሚኖሩበት ማሕበረሰብ ስለሚገኙ ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች የሚገልፅ መረጃ፥ እና
    - በክልከላው ካልተስማሙ ይግባኝ የመጠየቅ መብቶ

3. ጎጂ ጥቅም ውሳኔዎ ስለ እያገኙ ስላሉት አገልግሎቶች ከሆነ ይግባኞ እስኪወሰን አገል ግሎቶቹ እንዲቀጥሉ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የሚያገኙትን ጥቅም ጥቅም እንዲቀጥል የሚ ፈልጉ ከሆነ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርብዎታል፡-
    - የጎጂ ጥቅም ውሳኔው በደረሶ በ10 ቀናት ውስጥ ጥቅሞች ማስቀጠያ የመጠየቅ ግዴታ አለቦ.
    - የይግባኝ ጥያቄዎ ተቀባይነት ካጣ ለቀጠለው አገልግሎት እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ።

4. BHO በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ የይግባኝ ጥያቄዎ እንደደረሰው ያሳውቅዎታል።

5. በይግባኝ ሂደቱ ወቅት የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- በይግባኙ ሂደት ላይ ይረዳኛል የሚሉትን ሕጋዊ ተወካይዎን፥ በምስጢር ጉዳይ የሚሰማን አካል፥ ሌላ ጠበቃ፥ ወይም ማንኛውንም ሰው። እርሶን ለሚወከል የውክልና ስልጣኑ በፅሁፍ መሆን አለበት፡፡
- ሊረዳዎት የሚችል ማንኛውንም ማስረጃ።
- የሕክምና ሰነድዎን ጨምሮ የይግባኝ ሂደቱን ክፍል የሆነ የጉዳይዎ ፋይል፥ ማንኛውንም ሌላ ሰነድ እና መዝገቦች ማየት።

6. የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ማራዘሚያ ጊዜ ካልተሰጠው በስተቀር፥ የይግባኝ ጥያቄዎ እንደደረሰው በ 30 ቀን ውስጥ ውሳኔ ያደርጋል።

7. እርስዎ ወይም የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ለእርስዎ የሚበጅ ከሆነ ተጨማሪ 14 የማራዘሚያ ቀን መጠየቅ ይቻላል። የፀባይ ጤና ድርጅት BHO የማራዘሚያውን ጊዜ ከጠየቀ፥ ይህ ይነገርዎታል።



## የተፋጠነ ይግባኝ ምንድን ነው?

እርስዎ ወይም የፀባይ ጤና አገልግሎት ሰጪዎ ለፀባይ ጤናዎ አስፈላጊ እንደሆነ ከተሰማ ችሁ፥ የተፋጠነ ይግባኝ መጠየቅ ትችላላችሁ። የፀባይ ጤና ድርጅት BHO በዚህ ከተስ ማማ፥ በአካል ወይም በስልክ ይነገርዎታል። ጉዳዮ በፍጥነት እንዲፈታ በተፋጠና ሁኔታ የመታየት ሁኔታን ካሟሉ የእርሶ BHO በ72 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል:: የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ለእርስዎ አስፈላጊ እንደሆነ ከተሰማው፥ ሌላ ተጨማሪ 14 የማራዘሚያ ቀን ሊጠይቅ ይችላል።

## ስላቀረብኩት ይግባኝ የሚገልፅ ውሳኔ በጽሑፍ ይሰጠኛል?

ከፀባይ ጤና ድርጅት BHO ስላቀረቡት ይግባኝ ውሳኔውን እና ውሳኔው እንዲደረግ ስላስቻሉት ማስረጃዎች የሚገልጽ የውሳኔ ማሳወቂያ በጽሑፍ ይደርስዎታል። የይግባኙ ውሳኔ ለእርስዎ ካልተፈረደልዎ፥ ማሳወቂያው ጉዳይዎ በአስተዳደር በፍትሐዊ መንገድ እንዲታይልዎ የመጠየቅ መብት እንዳለዎት የሚገልጽ ይሆናል።

## የኔ ጉዳይ በአስተዳደር በፍትሐዊ መንገድ እንዲታይልኝ መጠየቅ የምችለውን እንዴት ነው?

የይግባኝ ሂደቱን ጨርሰውም በውሳኔው ካረኩ የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሶ በ120 ቀናት ውስጥ ለአስተዳደራዊ(ፍትሃዊ) መሰማት ለአስተዳደር ጉዳዮች ቅሬታ ሰሚ ፅ/ቤት እዚህ፡ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ::

Office of Administrative Hearings
PO Box 42489
Olympia, WA 98504
1-800-583-8271

የዚህን ቢሮ ዳኛ የቀረቡትን ማስረጃዎች አይቶ የዋሽንግተን ግዛት ሕግ ተጥሶ እንደሆን ውሳኔ ይሰጣል። የፀባይ ጤና ድርጅት BHO ውሳኔውን ማክበር ይኖርበታል። የቅሬታ ውሳኔ ላይ አስተዳደራዊ አቤቱታ መክፈት አይችሉም::

## መግለጫዎች

**አገልግሎት ማግኘት እስከ እንክብካቤ መስጠት ያለ መስፈርት፦** አንድ የMedicaid ተመዝጋቢ የባህሪ ጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት የግድ ማሟላት የሚገባው አነስተኛ የብቃት መስፈርቶች

**አስተዳደራዊ(ፍትሃዊ) መሰማት፡** የይግባኝ ሂደቱ ተመዝጋቢውን በሚያረካ መልኩ ጉዳዩን በማይፈታው ጊዜ በዋሽንግተን ግዛት የአስተዳደር ቅሬዎች ሰሚ ፅ/ቤት ስለሚደረግ መሰማት ፍትሃዊ መሰማት ተብሎ የሚታወቀው አስተዳደራዊ መሰማት.

**ጎጂ ጥቅም ውሳኔ፡**

1. በMedicaid የተሸፈነ አገልግሎት መከልከል ወይም በተወሰነ ደረጃ መፈቀድ ።
2. ከዚህ በፊት በፀባይ ጤና ድርጅት BHO ፍቃድ የተሰጠው አገልግሎት መቀነስ፥ ለጊዜው ማቋረጥ፥ ከነጭራሹ ማቋረጥ።
3. በBHO በሙሉ ወይም በከፊል ለአገልግሎት ክፍያ መከልከል።
4. በግዛቱ እንደ ተበየነው በBHO ወይም አገልግለት አቅራቢ በወቅቱ ለእርሶ አገልግሎት አለመስጠቱ
5. በDSHS ደንቦች እንደተበየነው ለቅሬታው ወይም ይግባኙ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ BHO ውሳኔ ሰይሰጥ መቅረቱ

**ይግባኝ፦** ጎጂ ጥቅም እርምጃ በድጋሚ እንዲታይ የሚቀርበው ጥያቄ

**የፀባይ ጤና እንክብካቤ፦** የአእምሮ ጤና እና/ወይም መድሃኒት የሚያስፈልገው ሕመም ሕክምና

**የፀባይ ጤና ኤጀንሲ (BHA):** በዋሽንግተን ግዛት የአዕምሮ ጤና እና በአደንዛዥ ዕፅ መጠቀም የተፈጠረ መዛባት አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ፍቃድ የተሰጠው እና ለዚህ ዓላማ ሲባል በንዑስ ተዋዋይነት በBHO የተቀጠረ ።

**የአደጋ ጊዜ አገልግሎት፡-** ከፀባይ ጤና ጋር የሚያያዝ የአደጋ ጊዜ በሚያጋጥመት ወቅት ለ24 ሰዓት የሚሰራ የምርመራና ግምገማ አገልግሎት። የአደጋ ጊዜ አገልግሎት፥ አደጋ ያጋጠመውን ሰው ለማረጋጋት፥ ተጨማሪ ችግር እንዳይደርስ ለማገት ቀልጣፋ ሕክምና በጣልቃ ገብነት ለመስጠት የሚያስችል አገልግሎት ነው፥ ይህም የሚሰጠው የግለሰቡን ሁኔታ በሚመች አከባቢ የሚሰጥ ሆኖ በተቻለ መጠን ከሚያስቸግር አከባቢ የራቀ ነው።

**ተመዝጋቢ፡-** Medicaid የተሸፈነ ሰው

**የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ፡-** አንድ ሰው ለራሱ፥ ለሌሎች አደጋ ውስጥ የሚያስገባ፥ ወይም እራሱ ላይ ከባድ አካል ጉዳት ሊያደርስ የሚችልና የአደጋ ጊዜ አገልግሎት ወይም የሆስፒታል ምርመራ ወደሚያስፈልገው ደረጃ እንዲደርስ የሚያደርገው ሆኔታ ላይ ከመድረሱ በፊት የሚሰጥ አገልግሎት።

**ድንገተኛ የጤና ሁኔታ:** ማለት፡ በቂ መጥፎነት ደረጃ ላይ በደረሰ ከፍተኛ ምልክት እራሱን የሚገልፅ ከባድ ህመምን ጨምሮ፤ስለጤና እና ህክምና አማካኝ እውቀት ባለው ጥንቁቅ ተራ ሰው እይታ አፋጣኝ የሆነ የህክምና ክትትል አለመኖር አለ ብሎ የሚገመት (ሀ) የግለሰቡን ወይም እርጉዝ ሴትን በተመለከተ የእሷን ወይም በሆዷ ያለውን ፅንስ ጤና አደገኛ ሁኔታ ውስጥ የሚከት (ለ) በሰውነት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ እክል ወይም (ሐ) ማንኛውም የሰውነት ብልት ወይም ክፍል ከፍተኛ የሆነ ብልሽት የጤና ሁኔታ (42 C.F.R. § 438.114(a)) **ለባህሪ ጤና ክብካቤ ፤ይህ በራስ ወይም በሌሎች ላይ ቅርብ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የመድረስ እድል አጋጣሚዎችን የሚያጠቃልል ወይም ከፍተኛ በሆነ የአእምሮ ጉድለት የሚመጣ ቅርብ አደጋ ተብሎ በተወከለ የአዕምሮ ጤና ባለሙያ ወይም የጤና ተከታታይ ሃኪም የተወሰነ::**

**ቅሬታ፡-** ጎጂ ጥቅም እርምጃ ያልሆነ ስለማንኛውም ነገር የሚሰማዋ ቅሬታ ቅሬታ፥ የእንክ ብካቤ ወይም የአገልግሎት ጥራት፥ የሰው ክብር አለመጠበቅ እና አገልግሎት ሰጪው የሚ ያጓድለው አክብሮት፥ ወይም የመብት አለመበጠበቅ የሚያካትት ቢሆንም በሱ የሚወሰን ግን አይደለም።

**የሕክምና አስፈላጊነት፡-** የተጠየቀውን አገልግሎት የሚገልጽ እና እተባባሰ የሚሄደውን የባለጉዳዩን ሁኔታ የሚገታ፥ ሕመሙ ለይቶ እንዲታወቅ የሚረዳ፥ የሚያስተካክል፥ የሚ ያድን፥ ከሕመሙ የሚገላግል ወይ ከሕመሙ የሚጠብቅ። አለበለዚያ የሕመምተኛውን ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥል ወይም ስቃይ የሚያመጣ፥ ወይም ሕመምና የአካል ጉዳት የሚያደርስ፥ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት እና መዛባት የሚመጣ ይሆናል። እንዲህ መደረግ የሚኖርበት ለሕመምተኛው የሚሆን ሌላ ጥሩ ውጤት ያለው፥ ይበልጥ ወጪ የማያስ ወጣ፥ ወይም ትንሽ ወጪ ያለው ሕክምና ማግኘት ካልተቻለ ነው። ይህ የሕክምና ዓይነት ሌላ ተጨማሪ ማከም ሳያስፈልግ በማየት ብቻ የሚያልቅ ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨ ማሪ ግለሰቡ 1) በዋሽንግተን ግዛት የህዝብ የፀባይ ጤና አገልግሎት የሚሰጥ የፀባይ ጤና አገልግሎት እንዲሰጠው ፍቃደኛ መሆን፥ 2) የግለሰቡ የአካል ጉዳት እና ከሱ ጋር የሚይ ያዙት ነገሮች በፀባይ ጤና እክል ያጋጠመ ሊሆን ይገባል፥ 3) ጣልቃ ገብነቱ በፀባይ ጤና እክል ምክንያት ያጋጠመውን ሁኔታ የሚያሻሽል፥ የሚያረጋጋ፥ ወይም እንዳያጋጥም የሚ ከለክል መሆን አለበት፥ 4) ግለሰቡ ከጣልቃ ገብነቱ ጥቅም ማግኘት ይኖርበታል፥ እና 5) ሌላ ማንኛውም መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ ስርዓት ወይም ድጋፍ የግለሰቡን ያልተ ሟላ ፍላጎት የሚፈጽም ካልሆነ።

**ጎጂ ጥቅም እርምጃ ማስታወቂያ ከላይ** ትርጉም እንደተሰጠው BHO ለተመዝጋቢ ጎጂ ጥቅም እርምጃን እንዲያሳውቅ የሚሰጠው የፅሁፍ ማስታወቂያ

**በምስጢር ጉዳይ የሚሰማን አካል የሚሰጠው አገልግሎት፡-** ከባህሪ ጤና አገልግሎትዋ ጋር በተያያዘ ቅሬታ፤የይግባኝ ፥ ወይም ጉዳይዎ በአስተዳደር በፍትሐዊ መንገድ እንዲታ ይልዎ ሲፈልጉ የሚረዳ በነፃ የሚሰጥና ምስጢርዎ የሚጠበቅበት አገልግሎት። በእንባ ጠባቂ አገልግሎት ውስጥ የሚሰራው ሰው፥ በቅርበት ጉዳይዎትን ወይም ችግርዎትን እንዲፈቱ ሊረዳዎት ይችላል። የእንባ ጠባቂው አገልግሎት ከ Behavioral Health Organization (BHO) ነፃ እና የባህሪ ጤና አገልግሎት ባገኘ ሰው ወይም የቤተሰብ አባል የሚሰጥ ነው፡፡

**ድህረ-ማገገም አገልግሎት፡-** የግለሰቡ የጤና ሁኔታ በቂ በሆነ መልኩ ከተረጋጋ በኃላ ወይም ያለችግር ሊወጣ/ልትወጣ ወይም ወደ ሌላ የህክምና ተቋም ሊዘዋወር ሲችል/ ስትችል ከአስቸኳይ የህክምና ሁኔታ የተያያዙ በህክምና አስፈላጊ አገልግሎት የሆኑ አገልግሎቶች

**ማገገም፡-** ግለሰቦች ጤናቸውን እና ደህንነታቸውን የሚያሻሽሉበት እራስ መር ህይወት የሚኖሩበት የለውጥ ሂደት

**የአገልግሎት ጥያቄ፡-** አገልግሎቶች ሲፈለጉ ወይም አገልግሎቶቹን ለማግኘት ጥያቄ በ BHO ወይም በአገናይ ኤጀንሲ በኩል በስልክ ፤በአካል ወይም በተመዝጋቢው ወይም በህግ ለህክምና አገልግሎት ስምምነት ሊሰጥ በሚችል ሰው በፅሁፍ ሲቀርብ::

**አጣዳፊ እንክብካቤ፡-** የፅባይ ጤና አደጋ አፋፍ ላይ ለሚገኝ ግለሰብ የሚሰጥ አገልግሎት። አገልግሎቱ ጥያቄው በቀረበ በ24 ሰዓት ውስጥ ማግኘት ካልተቻለ፥ የግለሰቡ ሁኔታ ሊባባ ስና ድንገተኛ እንክብካቤ ወደሚያስፈልግበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል።

## መግለጫ፡-

## ዓላማችን፡-

ተደራሽነት ያለው የምገገም፥ ራስን ወደ መቻል የሚያደርስና ጤናን የሚመልስ አገልግሎት በመስጠት ሕይወትን መለወጥ ነው።

Washington State Department of Social & Health Services

Transforming lives

DSHS 22-661 AM (Rev. 10/17) Amharic